# የጥያቄ መልስ

ታቦትን አስመልክቶ ዲ/ዘመንፈስ ክአርሲ ለጠየቁን ጥያቄ የተሰጠ መልስ።

ትምህርተ ሃይማኖት (የሃይማኖት ትምህርት) በሁለት ይከፈላል ። ይኸውም

1ኛ. ዶግማ ፤ 2ኛ. ቀኖና በሚል ነው።

ዶግማ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ፍቼም እምነት ማለት ነው።

ቀኖና ደግሞ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ሥርዓት ማለት ነው። ከነዚህ ከሁለቱ ዶግማ ወይም እምነት አይጨመርበትም፣ አይቀነስለትም፣ አይሻሻልም፣ ችግርና ፈተናም ቢመጣ እስከሞት ድረስ አጥብቀን የምንይዘው ነው። ለምሳሌ ያህል ይህን ዓለም ከአለመኖር ወደመኖር አምጥቶ የፈጠረ ቢመረምር እንጂ የማይመረመር ሁሉን ቻይ አምላክ የሚሳነው ነገር የሌለ ፈጣሪ፣ የሰማይና የምድር ባለቤት የሠራዊት ጌታ ሕያው እግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር (ፈጣሪ) የአካል ሦስትነት አለው። በመለኮትና በመፍጠር በሥልጣን በፈቃድ ግን አንድ ነው።

በሦስትነቱ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ሲባል በአንድነቱ አንድ መለኮት አንድ እግዚአብሔር ይባላል። በአዳም ምክንያት ከመጣው የዘለዓለም ሞትና ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ የወጣነው ከሦስቱ አካላት በአንደኛው አካል ማለትም በውልድ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ ዶግማ ወይም እምነት ይባላል።

ቀኖና ግን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስ ቶስ እምነው ያደጉ ክርስቲያኖች የሚመሩበት ሥርዓት ስለሆነ፣ በሃይማኖት አባቶች ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት እንደጊዜው ሁኔታ የሚሻሻል በመሆኑ የሚጨመርበት የሚቀነስለት ነው። ለምሳሌ ያህል እኛ ኦርቶዶክሳውያን ስንጠመቅ ሴት በሰማንያ ወንድ በአርባ ቀናችን ነው። የተወለዱት ሕፃናት ሴቷ ሰማንያ ወንዱም አርባ ቀን ሳይሞላቸው ቢታመሙና በሽታው እስኪ ከሆነ በ10፣ በ20፣ በ30...ቀናቸው መጠመቅ ይችላሉ ቀኖና ነውና። በቤተ ክርስቲያናችን የቀዳስያን ብዛት መነሻው አምስት ነው። ምናልባት ከአምስቱ አንዱ፣ ሁለቱ፣ ሦስቱ ቢታጡና ሌላም ተፈልጎ እስከ መጨረሻ የማይ ገኝ ከሆነ ከአቅም በላይም የሆነ ችግር ከገጠመ ሁለቱ ወይም አንዱ ብቻ ቀድሶ ማቁረብ ይች ላል። ቀኖና ነውና። በቤተ ክርስቲያናችን ታቦት ሲወጣ ቤተ ክርስቲያኑን የሚዞረው ሦስት ጊዜ ነው ችግር ካለ አንድ ጊዜ ብቻ ዞሮ መግባት ይችላል። ቀኖና ነውና በአጠ ቃላይ ሥርዓትን በተመለከተ ቀኖና ይባላል።

እምነትና ሥርዓትን ቅዱስ ጳውሎስ ለይቶ አስተምሮናል ለምሳሌ ያህል በቆላስይስ ሰዎች 2.ቁ.5 ላይ እንዲህ ይላል። «በሥጋ ምንም እንኳ ብርቅ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝና ሥርዓታችሁንም በክርስቶስም ያለውን የእምነታችሁን ጽናት እያየሁ ደስ ይለኛል» በዚህ ምንባብ ውስጥ በክርስቶስ የሆነው እምነት ዶግማ ሲባል ሥርዓት ብሎ የጠራው ቀኖናን ነው። ስለቀኖና (ስለሥርዓት) ቅዱስ ጳውሎስ ደጋግሞ ጽፏል። ከጻፈውም ውስጥ፤

1. «ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።» 1ቆሮ.14፥40።

2. «ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደተቀ በለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን። እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላ ችሁና» 2ተሰ.3፥6–7። ቀኖና (ሥርዓት) የሚወሰነው በሃይማኖት አባቶች እንደሆነና ወንጌልን የሚያስተምር ሰው ለሚያስተምራ ቸው ክርስቲያኖች በሃይማኖት አባቶች የተወሰነውን ቀኖና ማስተማርና መስጠት እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ያስረዳል።

በከተማዎችም ሲዞሩ በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች የቆረጡትን (የወሰኑትን) ሥርዓት ይጠብቁ ዘንድ ሰጧ ቸው። አብያተ ክርስቲያናትም በሃይማኖት ይበረቱ ነበር፣ በቁጥርም ዕለት ዕለት ይበዙ ነበር።» ይላል። የሐዋ.16፥4–5። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ቅዱስ ጳውሎስ ደርቤንና ልስጥራን በተባሉ ቦታዎች ለነበሩ ክርስቲያኖች ወንጌልን ከሰበከ በኋላ ሐዋርያት የወሰኑትን ቀኖና (ሥርዓት) እንደሰጣቸውና እናያለን። ይህም ሥርዓት በቁጥር አምስት ላይ እንደምናየው አብያተ ክርስቲያናት በሃይ ማኖት (በዶግማ) እንዲበረቱ፣ በቁጥርም ዕለት ዕለት እንዲበዙ እንዳደረገ እንረዳለን። ስለዚህ ቀኖና ወይም ሥርዓት ቤተክርስቲያንን ይጠቅ ማል እንጂ አይጎዳም። በመሆኑም ዶግማንና ቀኖናን ወይም እምነትንና ሥርዓትን ጎን ለጎን ይዞ መጓዝ ሐዋርያትን መከተል እንጂ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሁድን መከተል አይደለም። እንግዲህ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የሚቃ ወሙ ሰዎች ሁሉ፣ የሚቃወሙት በቀኖና (በሥርዓት) የሚመሩትን ክርስቲያኖች ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል የሆነ መጽሐፍ ቅዱስን በመሆኑ እንዳይሳሳቱ አደራ እንላለን።

አሁን እንግዲህ የዶግማንና የቀኖናን ልዩነት ከተረዳን በቀጥታ ወደ ታቦቱ ጥያቄ እንሄዳለን።

ጥያቄ– 1.ዛሬ በኛ ቤተ ክርስቲያን ያለው ታቦት ነውን? ወይስ ጽላት በታቦትና በጽላት መካከል ልዩነት አለና።

መልስ – ታቦት የጽላት ማስቀመጫ ነው። ዘጸ.40፥20። ጽላት ደግሞ ቅዱስ ቃሉ የተጻፈበት ቅዱስ ሰሌዳ ማለት ነው። ዘጸ.34፥27–28። ስለዚህ እነዚህ ሁለት ነገሮች ዛሬም በሐዲስ ኪዳን አሉ። ሆኖም ግን አሠራሩ ሙሉ በሙሉ በዘጸ.25፥10–18።

ያለውን የሙሴን ሕግ የተከተለ አይደለም። ምክንያቱም፥

1ኛ. ታቦት እንደሙሴ ሕግ የሚዘጋጀው ከግራር እንጨት ሆኖ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፤ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን ይልና በውስጥና በውጭም በጥሩ ወርቅ ለብጠው፤ በዙሪያውም የወርቅ አክሊል አድርግለት ይላል። ደግሞም ታቦቱን የሚሸከሙት ከወርቅ በተሠሩ መሎጊያዎች አራት ሰዎች እንደሆኑ እንረዳለን። በአጠቃላይ የብሉይ ኪዳን የታቦት አሠራር እጅግ ከባድ ነው። አይቻልም። ምናልባት አንዳንድ የቤተክርስቲያን ፍቅር የነበራቸው ያለፉት ነገሥታትና ዛሬም ፍቅረ ቤተክርስቲያን ያላቸው አንዳንድ ምእመናን ይችሉት እንደሆን ነው እንጂ።

2ኛ. ጽላት፥ ጽላትም እንደሙሴ ሕግ ከሆን መዘጋጀትና መጠረብ ያለበት ከድንጋይ ነው። በአንድ ታቦት ውስጥም መቀመጥ ያለባቸው ሁለት ጽላቶች ናቸው። ዘዳ.34፥1። በአጠቃላይ እንደብሉይ ኪዳኑ ሕግና ሥርዓት ከባድ ነው። የብሉይ ኪዳኑ ሥርዓትም ለሐዲስ ኪዳኑ ሥርዓት ጥላ ሆኖ አልፏል። 2ቆሮ.3፥7-11። ቆላ.2፥17። ዕብ.10፥1።

እንግዲህ እዚህ ላይ የሐዲስ ኪዳኑ ታቦትና ጽላት የብሉይ ኪዳኑን የታቦት አሠራርና ሥርዓት ጠንቅቆና ተከትሎ የማይሄድ ከሆነ፤ ይህ የብሉይ ኪዳኑን የታቦትና የጽላት አሠራር ሥርዓት ጠንቅቆ ያልሄደ የሐዲስ ኪዳን ታቦትና ጽላት ከየት መጣ? የሚል ጥያቄም ሳይነሳ አይቀርም።

እንባብያን ሆይ በቀጥታ ወደ ጥያቄው ከመግባታችን በፊት በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ ስለዶግማና ቀኖና ማብራሪያ የሰጠነው ይህን ለመሰለው ጥያቄ እንዲጠቅም ነው። አሁን ወደ ሐዲስ ኪዳን ታቦትና ጽላት ስንሄድ ቁም ነገሩ እንደሚከተለው ነው።

የሐዲስ ኪዳን ታቦትና ጽላት አሠራርም ሆነ አጠቃቀሙ የተወሰነውና የሚወሰነው በቀኖና ነው። ቀኖና ደግሞ እንደሁኔታው የሚሻሻል ነው። ሲቻል ይጨመርበታል ሳይቻል ደግሞ ይቀነስለታል። እንግዲህ በቤተክርስቲያናችን ቀኖና ካበረከተን ነገሮች አንዱ የሐዲስ ኪዳን የታቦትና የጽላት አሠራርንና አጠቃቀምን ነው።

ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን ታቦትን ለመሥራት የግራር እንጨት ባይገኝ በዘፍ.1፥31 ላይ «እግዚአብሔር የፈጠረውን (ያደረገውን) ሁሉ ተመለከተ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ» ስለሚልና እግዚአብሔር የፈጠረውን ስለማይገኝ ከግራር ሌላ ከማይነቅዝ እንጨት መሥራት እንችላለን። ቁመቱ ወርዱና ዙሪያውም እንደችሎታችን ይሆናል። በውስጥና በውጭ ስለሚሆነው የወርቅ ክብርም እንደችሎታችን ይሆናል። ከሌለንም ወርቁ ይቀራል ቀኖና ነውና።

ስለጽላቱም እንደዚሁ ነው ከቻልን ከክቡር ድንጋይ፥ ከዕብነ በረድ መቅረጽ እንችላለን፤ ካልቻልን ጽላቱን ከማይነቅዝ እንጨት መቅረጽ እንችላለን። በሌላ በኩልም ከቻልን እንደ ብሉይ ኪዳኑ በአንድ ታቦት ሁለት ጽላት ማስቀመጥ እንችላለን፤ ካልቻልን በአንድ ታቦት አንድ ጽላት ብቻ ይሆናል። በተጨማሪም የጽላቱን ማስቀመጫ ታቦት ባይኖረን ጽላቱን ታቦት ብለን በመጥራት በጽላቱ ብቻ መጠቀም እንችላለን። ቀኖና ነውና።

በዚህ ጊዜ ደግሞ በኤር.31፥31። 2ቆሮ.3፥1-3። በዕብ.8፥8-13። የኛ ሥጋ የእኛ ልቡና የእርሱ ታቦትና ጽላት አልሆነም ወይ? በሐዲስ ኪዳን ለምን ታቦትና ጽላት አስፈለገ? ለምንስ ይህ ሁሉ ችግር ተፈጠረ የሚሉ አሉ። ለዚህም በቁጥር አንድ መጽሔት ላይ እንደተገለጠው አዎ የኛ የክርስቲያኖች ልቡና በክርስቶስ ደም ታቦት፥ ጽላት፥ ቤተ መቅደስ መሆኑን እናምናለን። ቢሆንም በሐዲስ ኪዳን ታቦትና ጽላት ያስፈለገው ስለአምላካችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ሲባል ነው። ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ክብሩን የገለጠበት፥ ድምፁን ያሰማበት ሙሴን እንደባልጀራ ለማነጋገር የክብሩ ዙፋን ያደረገው ጽላቱ በውስጡ ያለበት ታቦቱ በመሆኑ፥ በሐዲስ ኪዳንም የሥጋውና የደሙ የክብር ዙፋን እንዲሆን ዞሮ ዞሮ ስለኛ በዓለም የተዋረደውን መድኅንዓለም ክርስቶስን ለማክበር ሲባል ነው።

ጥያቄ — 2. በዘዳ.31፥18፤32፥15-19።34፥1-5። 2ዜና.5፥10 ያሉትን ጥቅሶች በመጥቀስ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ሁለት ጽላቶችን ብቻ ነው። ነገር ግን የኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን እነዚህን አልፍ አእላፋት ጽላቶች ከየት አመጣቻቸው? አራብታችሁ ቅረጹ የሚል አለ ወይ?

መልስ — በዘዳ. 32፥19። ስንመለከት እግዚአብሔር ራሱ አዘጋጅቶ ለሙሴ የሰጠውን ሁለቱን ጽላቶች እሥራኤል ጣዖትን ሲያመልኩ ስላገኛቸው ሙሴ ተበሳጭቶ ሰበራቸው። ቸርነቱ ለዘለዓለም የሆነ አምላክ ሕያው እግዚአብሔርም ለሙሴ የመጀመሪያዎቹን አስመስሎ እንዲሠራ ነገረው። ሙሴም አስመስሎ ሠራ። ዘዳ.34፥1-5። መሥራት ብቻ ሳይሆን አሥሩን የቃል ኪዳን ቃላትም በጽላቶቹ ላይ እንዲጽፍ ሙሉ ሥልጣን ከእግዚአብሔር ተሰጠው። ሙሴም ተፈቅዶለታልና አሥሩን ቃላት በጽላቶቹ ላይ ጻፈ። ዘጸ.34፥27-28። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጽላትንም ሆነ ታቦትን እያስመሰሉ ለመሥራት ሙሉ ሥልጣንን አግኝተናል። ይህን በተመለከተ አንዳንድ አባቶች እንዲህ ይላሉ።

«አዳም እንኳን በደለ፤ አዳም ባይበድል ኖሮ አምላክ ሰው ሆኖ በቀራንዮ ስለእኛ የመሰቀሉን፥ ስለኛ የመሞቱን የፍቅር ምሥጢር እናውቀውም ነበር።

እሥራኤልም የጥጃ ምስል በሆነው በጣዖቱ እንኳን በደሉ እሥራኤል ባይበድሉ ሙሴ አይናደድም፤ በእግዚአብሔር የተዘጋጁት ሁለቱ ጽላት አይሠበሩም፤ የሰው ልጅም እግዚአብሔር የሠራቸውን የፊተኞቹን አስመስሎ ለመሥራት ሥልጣን ባልኖረውም፤ ቢሠራም ለምን ሠራህ ለሚለው መረጃ ባላቀረበም ነበር» ይላሉ። ያም ሆነ ይህ ጽላትን አስመስለን፥ አባዝተን፥ አራብተን ለመሥራት መሠረታችን ሥልጣኑ ለኛ ለልጆቹ የተላለፈልን ከአባታችን ሙሴ ነው።

ሙሴ የተሰበሩትን አስመስለህ ሁለት ጽላቶች ቅረጽ ከሚል በቀር ጽላቶችን አብዝታችሁ አራብታችሁ ተጠቀሙ የሚል ቀጥተኛ ቃል አምጡ ለሚለው ግን ነገሩ እንዲህ ነው። በብሉይ ኪዳን የጽላትም ሆነ የቤተመቅደስ ሥርዓት፤ የመስዋዕቱ የዕጣኑ አገልግሎት፤ በኢየሩሳሌም ብቻ ስለነበረና፤ የሌላውም አገር ሕዝብ የሚከተለው የጣዖትን

የገለጠላቸው ጥበብ ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ሕዝቡም እየተከተሉ ሰባት ጊዜ ግንቡን እንዲዞሩት ነው። የታዘዙትን አደረጉ ግንቡም ፈረሰላቸው። ኢያሱ.6፥1-17።

3. እሥራኤል ጠላት በበረታባቸው ጊዜ ጠላትን ለማሸነፍ ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ይወጡ ነበር። 1ሳሙ.5፥1-ፍ። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ካህናቱ ታቦቱን ከቦታ ወደቦታ ሲንቀሳቀሱ ካልሆነ በቀር ለሚፈልጉት አላማ ታቦቱን ካለበት ቦታ ተሸክመው አያወጡትም ነበር ማለት አንችልም። ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ ካስገባውም በኋላ ቢሆን ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው እንዳያወጡ የሚል ሕግም የለም። ቤተ መቅደሱ እስኪፈርስ ድረስም ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው አላወጡም የሚልም ደግሞ የለም።

ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ከቤተ መቅደስ እንደወጡ ምንባብ አለማግኘት ደግሞ በዚያ ቤተ መቅደስ ዘመን ሁሉ ታቦቱ አልወጣም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር የሠራው ሥራ በብሉይ ኪዳን የተፈጸመው አገልግሎት ሁሉ ሙሉ በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም። በመጽሐፍ ቅዱስም ያልተጻፈ ብዙ ነገር እንዳለ እናምናለንና በዚያም ሆነ በዚህ እኛ በሐዲስ ኪዳን ታቦትን ተሸክመን የምናወጣው፣

1ኛ. በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር ቸርነት (ትእዛዝ) ካህናቱ ታቦታቱን ተሸክመው እንዲወጡ ተደርጎ ካህናቱም ታቦቱን ተሸክመው በመውጣት በታቦቱ ያደረ ኃይለ እግዚአብሔር ለሕዝበ እሥራኤል ያደረገውን ድንቅ ሥራ ለማሰብና እግዚአብ ሔርን ለማመስገን ነው። ዛሬም ለሥጋና ለደሙ የክብር ዙፋን የሆነውን ቅዱስ ስሙም የተጻፈበትን ቅዱስ ታቦት በምናወጣበት ጊዜ በደሙ የባረከን መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ አሁንም የሥጋውና የደሙ ዙፋን በሆነው በታቦቱ ረቂቅ ኃይሉን በማስተላለፍ በረከቱን ያበዛልናል ብለን በማመን ነው።

የተሰቀለው አምላክ መከበሩና መንገሡ ቀርቶ በየጊዜው ታቦት ወጣ እየተባለ ታቦቱ ብቻ ነግሦ ከበረ ሕዝቡም ወደ አምልኮ ባዕድ ከበለለ ስለሚለው ግን አንድ ሕዝብ የንጉሡን ዙፋን ሲያከብርና ሲፈራ ንጉሡን ማክበሩና መፍራቱ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም።

እኛ የምናምነው ቅዱስ ስሙ የተጻፈበትን የክርስቶስ ሥጋና ደም የክብር ዙፋን የሆነውን ታቦት ማክበራችን በኪሩቤል ዙፋን የሚቀመጥ መድኅን ክርስቶስን ማክበራችን መሆኑን ነው። በታቦቱ ፊት መስገዳችንም በታቦቱ ለተጻፈው ለቅዱስ ስሙ ነው። በታቦት ፊት ለእግዚአብሔር ስም ይሰግዱ የነበሩ ኢያሱና የእሥራኤል ሽማግሌዎች በረከት አገኙበት እንጂ አልተጎዱም ኢያ.7፥6። ዘዳ.33፥10።

በሐዲስ ኪዳንም «ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፣ ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፣ በድንጋይም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፏል» ራእ.2፥17። ለዚህ ስም ደግሞ ጉልበት ሁሉ መንበርከክ እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

«በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» ፊልጵ.2፥10-11። በዚህ መሠረት ቅዱስ ስሙ በተጻፈበት ከነጭ ድንጋይ (ከዕብነ በረድ፣ ከእንጨት) በተሠራው በጽላቱ ፊት ለቅዱስ ስሙ መስገድ ታላቅ የመንፈስ ጥበብ እንጂ ሞኝነት አይደለም። ምናልባት ስለታቦት፣ ስለጽላት ባለማወቅ ባጠቃቀሙ በኩል የሚሳሳቱ አባቶች እና ቶች ካሉ ሸንጥን ጎትሮ ማስተማር ተገቢ ነው።

ከዚህ በላይ ስለ ታቦት ከቤተ መቅደስ መውጣትና አለመውጣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከመሆኑም በተጨማሪ ቀናና ቤተ ክርስቲያን መሆኑ መታወቅ አለበት።

ብዙዎች በሐዲስ ኪዳን ታቦትን ለመቃወም በኤር.3፥16። የተጻፈውን ጠቅሰው «ከእንግዲህ የእግዚአብሔር ታቦት ብላችሁ የማትጠሩበት ጊዜ ይመጣል» ተብሏልና ታቦት አያስፈልግም በማለት ያስተምራሉ። ምንም እንኳን ይህ ቃል የተነገረበትን ምክንያትና ትንቢቱም መፈጸሙን በቁጥር 1-እትማችን የገለጽን ቢሆንም አንድ ነገር መጨመሩ አስፈላጊ ይመስለናል።

እንደተባለው ታቦት ብሎ መጥራት ካላስ ፈለገ በኤርምያስ 31፥34። ደግሞ «እያን ዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፣ እያንዳንዱም ወንድሙን እግዚአብሔርን ዕወቅ ብሎ አያስተምርም!» ተብሎ የተጻፈ ስለአለ እንግ ዲህ ሰው ሁሉ በየዘመኑ እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ማስተማር አያስፈልግም ማለት ነዋ! ደግሞም ጌታችን በማቴ.28፥19። «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ» ብሎ መና ገሩ ስህተት መሆኑ ነዋ! በአጠቃላይ እንዲህ ነው ብሎ ከመናገር አስቀድሞ በመጽሐፍ የተጻፈው ነገር ለምንና እንዴት ባለሁኔታና ጊዜ መጻፉን ማጥናትና መልእክቱን (ምሥ ጢሩን) መመርመር ይገባል እንላለን።

በመጨረሻ ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማርያም፣ የገብር ኤል የጊዮርጊስ፣ ወዘተ. ታቦት እየተባለ የተሰየመበት ምክንያቱና የዚህ ስያሜ የትመጣው ምንድን ነው የሚሉ ጠያቂዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ እርግጥ ነው።

እንዲህ ተብሎ መሠየሙ በኢሳ.56፥4-6። በተገለጸው መሠረት የእግዚአብሔርን ሰንበቱን ለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘውንም ለሚ መርጡ ቃል ኪዳኑንም ለሚይዙ ጃንደረቦች (ስለእግዚአብሔር መንግሥት ራሳቸውን ጃንደረባ ያደረጉ ቅዱሳን) ማቴ.19፥12 በእግዚአብሔር ቤትና በቅጥሩ የዘለዓለም መታሰቢያ እንደሚደረግላቸው የተገለጠ በመሆኑና ይህን እብነት በማድረግ የጌታ ሥጋውና ደሙ የሚከብርበት ሆኖ ለቅዱሳኑም መታሰቢያ ለማድረግ ነው። የቅዱሳን መታሰቢያ ለዘለዓለም ነው። መዝ.111፥7። እንዲሁም የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነውና ምሳ.10፥7። በዚህ ምክንያት እንጂ በታቦታቱ የሚከብረው መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ መሆኑ ግልጽ ሊሆን ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ በቁጥር ሁለት እትማችን ስለ ጸበል በተጻፈበት ዓምድ ይህ የቅዱሳን መታሰቢያ በሰፊው የተገለጠ በመሆኑ ያንን ማንበብ ይጠቅማል።

እግዚአብሔር አስተዋይ ልቡና ይስጠን። ✣